12

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

አፍሪካ ቲቪ

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

# سُورَةُ البَيِّنَةِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

لَمۡ يَكُنِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ مُنفَكِّينَ حَتَّىٰ تَأۡتِيَهُمُ ٱلۡبَيِّنَةُ ١ رَسُولٞ مِّنَ ٱللَّهِ يَتۡلُواْ صُحُفٗا مُّطَهَّرَةٗ ٢
فِيهَا كُتُبٞ قَيِّمَةٞ ٣ وَمَا تَفَرَّقَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّا مِنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَةُ ٤ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ
مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلۡقَيِّمَةِ ٥ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ
أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ فِي نَارِ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَآۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ شَرُّ ٱلۡبَرِيَّةِ ٦ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ
وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ خَيۡرُ ٱلۡبَرِيَّةِ ٧ جَزَآؤُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن
تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُۚ ذَٰلِكَ لِمَنۡ خَشِيَ رَبَّهُۥ ٨



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## ሱረቱ አል-በይናህ

- (የግልፅ አስረጂዋ ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡
- የአናቅፁ ብዛት  (8) ናቸው፡፡

## ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-

- የነቢዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) መልዕክት ያለውን ደረጃ ግልፅነትና ምሉዕነትን የሚያሳይ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

# سورة البينة

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) አይሁዳዊያን፣ ነሳራዎች (ክርስቲያኖች) እና አጋሪ ከሀዲያን ግልፅ የሆነ መመሪያና ጉልህ የሆነ ማስረጃ  እስኪመጣላቸው ድረስ በክህደት ላይ ያላቸውን ስምምነትና የጋራ አቋም (ከነበሩበት አቋም) የሚላቀቁ አልነበሩም።
- (2) ይህ ግልፅ መመሪያና ጉልህ ማስረጃ ንፁህን እንጂ ማንም ሊነካው የማይገባውን ንፁህ መጽሐፍ ያነብላቸው ዘንድ ከአላህ የተላከ መልዕክተኛ ነው።
- (3) በዚህ መጽሐፍ ውስጥም እውነተኛ ንግግሮችና ሚዛናዊ ድንጋጌዎችን ያያዘ ሲሆን፥ የሰውን ልጅ ወደ ሚጠቅመውና ወደ ቀናው መንገድ የሚመሩ ናቸው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- (4) እነዚያ ተውራት የተሰጣቸው አይሁዳያዊያን እንዲሁም ኢንጂል የተሰጣቸው ነሷራዎች ለመለያየት የበቁት አላህ መልዕክተኛውን ከላከላቸው በኋላ ነው። ከነሱ እስልምናን የተቀበለ አለ፤ የነቢዩን እውነተኝነት እያወቀ በክህደቱ ላይ የቀጠለም አለ።
- (5) የአይሁዳዊያን እና የነሷራዎች ግትርተኝነት እና ወንጀለኛ መሆናቸውን የሚያጎላው ነገር እነሱ በቁርኣን የታዘዙት በመጻሕፍቶቸው የታዘዙትን እንጂ የተለየ ነገር አለመታዘዙ ነው። ያም ትዕዛዝ አላህን በአምልኮቱ ላይ ምንም ሳያጋሩ እሱን ብቻ እንዲገዙ፣ ሰላትን እንዲያቋቁሙ እና ዘካ እንዲያወጡ ነው። የታዘዙትም ምንም ጎባጣ የሌለውን ቅኑን ሃይማኖትን ነው። (ይህም የቀጥተኛይቱ ሃይማኖት ድንጋጌ ነው፡፡)



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- (6) እነዚያ አላህን የካዱ አይሁዳዊያን፣ ክርስቲያኖች እና አጋሪያን በትንሳኤው ቀን ዘውታሪዎች ሲሆኑ ጀሀነም እሳት ውስጥ ለዘላለም ይኖራሉ። በክህደታቸውና መልዕክተኛውን በማስተባበላቸው ምክንያት ከፍጥረታቱ ሁሉ ከፉዎች ናቸው።
- (7) እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ እነሱ ከፍጥረታት ሁሉ በላጮች (ምርጦች) ናቸው።

- (8) ምንዳቸው ጌታቸው ዘንድ ሲሆን እርሱም ከህንፃዎቹና ከዛፎቹ ሥር ወንዞች የሚፈሱባቸው የሆኑ ጀነቶች ናቸው። በውስጧም ለዘለዓለም ነዋሪዎች ናቸው። በአላህ በማመናቸውና ለእርሱ ታዛዥ በመሆናቸውም የተነሳ አላህ ወዷቸዋል። የአላህ እዝነትም ስለገጠማቸው በስጦታው ረክተዋል። (አላህ ከእነርሱ ስራቸውን ወደደላቸው፡፡ ከእርሱም ምንዳውን ወደዱ፡፡) ይህችን እዝነት የሚያገኞት ጌታውን በመፍራት ትዕዛዛቱን የፈጸፀመና የከለከለውን የራቀ ሰው ነው።

## ከሱረቱ አል-በይናህ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ከሀዲያን ከፍጥረታት ሁሉ መጥፎ ፍጡሮች ሲሆኑ አማኞች ደግሞ ከፍጥረታት ሁሉ መልካም ፍጡሮች መሆናቸውን።
2. የሃይማኖቶች በመሠረታዊ እምነት ላይ አንድ ዓይነት አቋም መኖር መልዕክትን ለመቀበል መዕሠረታዊ መነሻ መሆኑን።
3. ኢስላም በመጣበት ዘመን የነበሩት ልዩ ልዩ እምነቶች የተለዋወጡና እውነትና ውሸት የተደባለቀባቸው እንደነበሩ፤
4. የመፅሐፍ ባለቤቶች የነብዩን መላክ በተስፋ ይጠብቁት እንደነበርና ሲላኩ ግን ከፊሎች አምነው ከፊሎቹ እንደካዱ፤



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## ከሱረቱ አል-በይናህ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-

5. የመፅሐፍ ባለቤቶች በመፅሐፋቸው ከታዘዙት መካከል ሽርክና ኩፍርን ወደ ጎን በመተው አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ፣ ሶላት እንዲሰግዱና ዘካ እንዲሰጡ ሲሆን ለምን ይህን ተግብሩ ሲባሉ አንደ አመፁ፤
6. ትክክለኛው እምነትና ነፃ የሚያወጣው መንገድ አላህን በብቸኝነት ማምለክና ሶላት መስገድ ዘካ መስጠት መሆኑን፤
7. በኢስላም የካደ ሰው ምንዳው ከሁሉም የከፋ መሆኑን፤
8. ኢስላምን ተቀበሎ ለአሏህ ትዕዛዝ ያደረ ምንዳው ጀነት እንደሆነ፤
9. አላህን መፍራት ምን ያህል መልካም ስነ ምግባር እንደሆነ፤
10. ከሓዲያን ካፊሮች ከከብቶችና ከእንሰሳዎች በታች መሆናቸውን እንማራለን፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com